Takoma Park Recreation Department
301-891-7290 takomaparkmd.gov/recreation

# የ 2024 ፉትሳል ሊግ ህጎች

1. **የደህንነት ቅድመ ጥንቃቄ እርምጃዎች፦** ሊጉ CDC እና DHHS ያወጣው ወቅታዊ የኮቪድ መመሪያዎችን ይከተላል። አሁን ላይ ሁሉም ተሳታፊዎች፣ ተመልካቾች እና አሰልጣኞች ግጥሚያዎች እና ልምምዶች ላይ በሚታደሙበት ወቅት የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል እንዲያደርጉ አይገደዱም። በተጨማሪም፣ ክትባቱን ለመውሰድ ብቁ የሆኑ ሰዎች ሁሉ ክትባቱን እንዲወስዱ እናበረታታለን፣ ነገር ግን ይህ ለመሳተፍ እንደ ቅድመ ሁኔታ አይጠየቅም።
2. **የጨዋታ ግጥሚያ**
   a. የግጥሚያው ርዝመት ሳያቋርጥ በሚቆጥር ሰዓት ሲለካ ሁለት (2) ባለ ሃያ (20) ደቂቃ የጨዋታ አጋማሾችን ይይዛል። በሁለቱ አጋማሾች መካከል የአምስት (5) ደቂቃ የዕረፍት ጊዜ ይኖራል።
   b. ሰዓቱ መቁጠር የሚያቆመው የዕረፍት ሰዓት ሲደርስ፣ ጉዳት ሲያጋጥም እና በሁለተኛው አጋማሽ የመጨረሻ አንድ (1) ደቂቃ ላይ በሚሰማ ማንኛውም የፊሽካ ድምፅ ብቻ ይሆናል።
   c. ከመደበኛው የጨዋታ ጊዜ ገደብ በላይ የሚኖር የተጨማሪ ደቂቃ ጨዋታ የጊዜ ገደብ 3 ደቂቃ መሆን አለበት። ሰዓቱ እስከ ጨዋታው የመጨረሻው ደቂቃ ድረስ መቁጠር አይቆምም። ከሁለተኛው (2ኛ) መደበኛ የጨዋታ ጊዜ በላይ የሚኖር የተጨማሪ ደቂቃ ጨዋታ የጊዜ ገደብ የድንገተኛ ሞት (sudden death) የጨዋታ ጊዜ ይሆናል።
   d. በተጋጣሚ ቡድኖች መካከል ያለው የውጤት ልዩነት ከ 7 ጎሎች በላይ ከሆነ ውጤቱ ወደ 0 - 0 እንዲመለስ የሚደረግ ሲሆን ይህም ህግ እስከ ጨዋታው መጨረሻ ድረስ በተደጋጋሚ ሊተገበር ይችላል።
   e. ዳኞች/ለጨዋታው የተመደቡ አመራሮች (Officials) በተሳታፊዎች ሁሉን አቀፍ ዕድገት ላይ እንዲሁም በልጆች መዝናናት መቻል ላይ የበለጠ ትኩረት ያደርጋሉ
2. **የጨዋታ ህጎች**
   a. ሳንቲም ሲጣል የሳንቲሙን ትክክለኛ ጎን/ገፅ በመጥራት ያሸነፈው ቡድን ጨዋታው ሲጀመር ኳስ እንደነካ ወዴት አቅጣጫ እንደሚያጠቃ (እንደሚጫወት) ይወስናል።
   b. ከግብ ጠባቂ በስተቀር ሌሎች ተጨዋቾች ኳስ በእጅ መንካት አይፈቀድላቸውም፣ ግብ ጠባቂውም በእጅ መንካት የሚፈቀድለት በጎል ሳጥን ውስጥ ሲሆን ብቻ ይሆናል።
   c. ግብ ጠባቂዎች ኳስ በእጅ በመወርወር እንጂ በእግር በመመታት ማቀበል አይችሉም። ግብ ጠባቂው የሚወረውረው ኳስ ግብ ጠባቂው ከሚገኝበት የሜዳ አጋማሽ ወሰን ውጪ/በላይ ማረፍ አይችልም። ኳሱ ከሜዳው አጋማሽ ½ ምልክት በፊት መንጠር አለበት።
   d. ኳሱ ከመጫወቻ ሜዳ ወሰን/መስመር ውጪ ካልወጣ፣ ጣሪያ ወይም የቅርጫት ኳስ አምድ (hoop) ካልነካ በስተቀር ኳሱ በጨዋታ ውስጥ ሆኖ ይቆያል። ኳሱ ወደ ጨዋታ የሚመለሰው በተቃራኒ የተጋጣሚ ቡድን “የመልስ ምት” ይሆናል።
   e. የፍፁም ቅጣት ምቶች **<u>አይኖሩም</u>**።
   f. የቅጣት ምቶች ይኖራሉ

3. **አፍታ የዕረፍትጊዜ**
    a. በአንድ ጨዋታ ሶስት (3) ባለ ሠላሳ ሰከንድ የአፍታ ዕረፍት ጊዜዎች ይኖራሉ። ጨዋታው በመደበኛው የጨዋታ ጊዜ ገደብ ከተጠናቀቀ ጥቅም ላይ ያልዋሉ የአፍታ ዕረፍት ጊዜዎች ወደ ተጨማሪ የጨዋታ ሰዓቶች አይተላለፉም። ከመደበኛው የጨዋታ ጊዜ ገደብ ውጪ በሚኖር ተጨማሪ የጨዋታ ሰዓት አንድ (1) የአፍታ ዕረፍት ጊዜ ይኖራል።
4. **ማሊያዎች**
    a. በቡድን ውስጥ ያሉ ሁሉም ተጫዋቾች ውድድሩን በሚያዘጋጀው ሊግ በሚሰጥ አቅጣጫ መሰረት አንድ አይነት ቀለም ያላቸው የቡድን ማሊያዎችን መልበስ አለባቸው፣ በጨዋታው ወቅት ሁሉም ተጫዋቾች የቅልጥም መከላከያዎችን( shin guards) ማድረግ አለባቸ።
5. **በጨዋታው ላይ የሚሳተፉ የተጫዋቾች መጠን(ROSTER SIZE)**
    a. በጨዋታው ላይ የሚሳተፉት 10 የተጫዋች ሲሆኑ፤ ግጥሚያው 5 ለ 5 የሚደረግ ይሆናል (4 የሜዳ ተጫዋቾች እና 1 ግብ ጠባቂ)
6. **የእሮይታጊዜ**
    a. የዕለቱ መጀመሪ ጨዋታ ከመጀመሩ አስቀድሞ የ 5-ደቂቃ የቅድመ ዝግጅት እሮይታ ጊዜ ሊኖር ይገባል። የአንድ ቡድን ዝቅተኛ የተጫዋቾች ብዛት (4) በመጫወቻ ሜዳ ውስጥ ከተገኙ ቡድኑ ጨዋታውን በታቀደለት ጊዜ መጀመር አለበት። የጨዋታው አዘጋጅ ሰራተኞች በጨዋታ ደንብ መጣስ (forfeited games) ምክንያት የሚተላለፍ የመጨረሻ ውሳኔ የማስተላለፍ ኃላፊነትን ይወስዳሉ።

7. **በጨዋታ ላይ የሚፈፀሙ ጥፋቶች**
    a. በጨዋታ ላይ የሚፈፀሙ ሁሉም ጥፋቶች ቀጥተኛ ያልሆነ የቅጣት ምት ያስከትላሉ። ኳሱ ወደ ጨዋታ ከመመለሱ በፊት ቀጥተኛ ያልሆኑ ቅጣት ምቶች ለቡድን ጓደኛ አሳልፎ/በመስጠት መጀመር አለባቸው።
8. **የተጫዋች ቅያሪዎች**
    - የተጫዋች ቅያሬ ቁጥር ገደብ የለውም እንዲሁም ጨዋታው በሂደት ላይ እያለ ማቋረጥ ሳያስፈልግ የተጫዋች ለውጥ ማድረግ ይቻላል፣ ነገር ግን ወደ ጨዋታው የሚገባው ተጫዋች ተቀይሮ ከሜዳው የሚወጣው ተጫዋች ሙሉ በሙሉ ከሜዳ ሳይወጣ መግባት አይችልም።
9. **መጥፎ የአየር ሁኔታ**
    - መጥፎ የአየር ሁኔታ በሚከሰትበት ጊዜ የጨዋታ መርሀ ግብሮችን ለማሰረዝ እባክዎን ወደ በመዝናኛ መምሪያ (Recreation Department) የመጥፎ አየር ሁኔታ ማሳወቂያ የጥሪ መስመር ቁጥር (301-891-7101 ext. 5605) ይደውሉ።